Institute of Development & Education for Africa, Inc.

webmaster@africanidea.org 1199 Whitney Ave Suite 523, Hamden, Ct, USA 06517

ታሕሳስ 27 2006 January 6, 2014

## ይድረስ ለኢትዮጵያውያን ሁሉ በያላችሁበት፡ ለአዲስ ዓመት አዲስ ርእዮተዓለም

ገላውዴዎስ ኣርኣያ

አዲስ ዓመት የምንለው ከሃገራቸው ተሰደው በባዕድ አገሮች ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንጂ በሃገር ውስጥ ለሚኖሩ ወገኖቻችን አይደለም። ስለዚህም ይህ ጽሑፍ ከሞላ ጎደል ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያንን የሚመለከት ሆኖ ግን በከፊልም ቢሆን አገር ቤት ላሉትም መልእክት ለማስተላለፍ አንዱ ዓላማው ነው። አዲስ ርእዮተዓለም ማለት ደግሞ በቀድሞው አነጋገር ወይም ዘይቤ አይድዮሎጂ ማለታችን ሳይሆን በቀጥታ ትርጉሙ ‘አዲስ አስተሳሰብ ወይም አመለካከት፣ ነገር ግን አድማሳዊ ተቀባይነት ያለው’ ለማለት ነው። ርእዮተዓለሙ በአካለመጠን ወይም በአብዛኛው ሕዝብ ተቀባይነት እንድያገኝ ከተፈለገ ግን መጀመርያ ተሳታፊው ሕዝብ በቀና መንፈስ ነገሮችን መፈተሽ አለበት፣ አወንታዊ መንፈስ ይዞም መነሳት ይኖርበታል።

የአወንታዊ ስሜት አመለካከት የመጀመርያ መምህር ታ ሆተፕ የሚባል በጥንታዊቷ ከመት ወይም ግብጽ የነበረ ፈላስፋ ነው። ታ ሆተፕ በአምስተኛው ስርወ መንግሥት (2450-2300 ዓመተ-ዓለም) ጊዜ የነበረ ታዋቂ ሊቅ ሲሆን በስሙ የሚጠራ መጽሐፈ-ታ ሆተፕ በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ ‘መዓት’ የተባለውን የከመት ወይም የጥንታዊት ግብጽ ስነ-ሐሳብ ለመጀመርያ ጊዜ ያስተዋወቀ ነው። ‘መዓት’ በኛው ቋንቋ አሉታዊ ትርጉም ነው ያለው፣ ለሚከሰተው መጥፎ ነገር ሁሉ ‘መዓት’ እንለዋለን። በግብጻውያን ስነ-ሐሳብ ግን ‘መዓት’ ማለት ሐቅ ፣ፍትሕ ፣ሚዛን ፣ስምምነት፣ ጸጥታ፣ ደንብ እና ውለታ፣ ያካተተና ሰፊ ትርጉም ያለው ቃል ነው። ይህ የመዓት አስተሳሰብ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት ስለነበረው ደግሞ ሕበረተሰቡ በፍትሕ የተገዛና ጸጥታና እርጋታን የተጎናጸፈ ሕብረተሰብ ነበር ማለት ይቻላል። ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸውን የከተማና የከፍላተ-ሃገራት ገዢዎች፡ እንዲሁም የብሔረ-መንግሥት መሪ የሆነውን ፈርዖን ሳይቀር በመዓት አገራቸውን እንዲገዙና ሕዝባቸውን እንድያስተዳድሩ ይጠበቅባቸው ነበር።

ለዚሁ ጽሑፍ አግባብነት ያለው የ ታ ሆተፕ አመለካከት ግን ከፍ ብለን የጠቀስነውን የመዓት መሠረተ-ሐሳብ ወይም መርሆ ብቻ ሳይሆን ፈላስፋው ስለ ጠቢብ (አዋቂ) እና ስለ ሞኝ ሰዎች የተናገረውን ነው። እንዲህም ይላል። “ጠቢብ ሰው በጠዋት የሚነሳው ራሱን ለማቋቋም ሲሆን፣ ሞኝ ሰው ግን በጠዋት የሚነሳው ራሱን ለማናወጽ ነው”። ባጭሩ፡ ጠቢቡ አወንታዊ ኃይል ሲሆን፣ ሞኙ ደግሞ አሉታዊ ኃይል ነው። ስለሆነም በዚሁ ጽሑፍ ለሚቀርቡ ልዩ ልዩ ዓበይት ነጥቦችና ቁምነገር-አዘል ርእሰ-ነገሮችና ገንቢ ነቀፌታዎች በጥሞና አይተን ከተጨባጭ የኢትዮጵያ ሁኔታዎች ጋር ማገናዘብ ከፈለግን እንደ ጠቢቡ ሰውየ በጠዋት አወንታዊ መንፈስ ይዘን መነሳት አለብን።

ባለፉት ሁለት አሰርት ዓመታት እኔ በበኩሌ መጻሕፍትና በርካታ ትምህርታዊ ድርሰቶችን አበርክቻለሁ። እንዲህ ማለቴ ግን ስለራሴ ለመናገር ወይም ስላደረግኋቸው ነገሮች ለመደንፋት ሳይሆን በተቃራኒው በቅርብ የማውቃቸው ጓደኞቼና የስራ ባልደረቦቼ መጻሕፍት እንድያበረክቱ ጥረት አድርግያለሁ ለማለት ብቻ ነው። ግን የኔ ድጋፍ ብቻ ሳይሆን በራስ አነሳሽነት መጻሕፍት ያቀረቡልን እንደ ዳንኤል ግዛው እና አያሌው ይማም ለመሳሰሉ ደራስያን ላደረጉት በጎ ጅምር በይበልጥ ለማጎልመስ ደግሞ ለመጻሕፍቶቻቸው መቅድም (foreword) እና የመጽሐፍ ጀርባ አስተያየት (blurb) ወይም በአርትኦት ስራ በመተባበር ረድቻቼዋለሁ። ሌሎች ደራስያን እንደ አስማማው ኃይሉ፣ መአዛ መንግስቴ፣ ስዩም ሐረጎት፣ ቡልቻ ደመቅሳ፣ ሂወት ተፈራ እና ካሕሳይ አብርሃ ለመሳሰሉት ደግሞ ለመጻሕፍቶቻቸው አቃቂር በመጻፍ ተባብሬአቸዋለሁ። ገዴዎን ወልደ አማኑኤል በቅርብ ጊዜ Game Changers of Identity Politics in Ethiopia በሚል ርእስ አሳትሞ ያወጣውን መጽሐፍ የኔ አንድ ጽሑፍ ይገኝበታል። መጽሐፉ ከመታተሙ በፊት ግን ገዴዎን የኔን ጽሑፍ ለማከል ፈቃድ ጠየቀ፣ እኔም በደስታ ተቀበልኩት። ሰለሞን ገብረስላሴ ደግሞ በቅርብ ጊዜ በRed Sea Press ታትሞ የሚወጣውን እና እኔም የጀርባ አስተያየት የጻፍኩለትን EPRP: Between A Rock and A Hard Place: A Brief History of the Ethiopian Peoples Revolutionary Party የተሰኘውን ግሩም መጽሐፍ ደርሷል።

ከነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸውን ደራስያን አብዛኞቹ ከማመስገን አልፈው የመንፈስ ብርታት እንዲኖረኝም አድርገዋል፣ አንድ ሁለት የሚሆኑ ግን የጅል ስሕተት በመስራት የ ታ ሆተፕ ውለታ ከማድረግ ይልቅ በተቃራኒው በማዠረፍ እኔን ለማጥላላት እና የጽሑፍ ስራዎቼን ለማጉደፍ መኩረዋል፣ ያጕረሰውን እጅ እንደመንከስ ማለት ነው። ነገር ግን ለነዚህ ግለሰቦች አልተቀየምኳቸውም፣ ይቅር ብያቸዋለሁ፣ የ ታ ሆተፕ ስነምግባርም እንዲከሰትላቸው እመኝላቸዋለሁ።

የሰው ልጅ ከሁሉም እንስሳት የሚለዩት አንድ ነገር ቢኖር ጠቢብ የመሆን ችሎታው ነው። ፣ ፍላጎት ካለና አወንታዊ አመለካከት ከተጨመረበት ደግሞ ጠዋት ተነስቶ ራሱን ለማቋቋም የሚጣጣር ሁሉ ግቡን እንደሚመታ ወይም ያቀደውን ነገር እንደሚሳካለት የታወቀ ነው። እንግዲህ ጠቢባን ለመሆን እምቅ ኃይል ካለን ተአምር መስራትም እንችላለን ማለት ነው። ነገር ግን ከታሪክ ውስብስብነትና ሕብረተሰባዊ ውጥንቅጥነት አንጻር ካየነው ደግሞ ግባችን ለመምታት በምንጓዝበት ጊዜ መሰናክሎች እንደሚያጋጥሙን መገንዘብ አለብን። ይኸንን በግምት በማስገባት ነው እንግዲህ የሚከተሉትን ርእሰ-ነገሮች ለውይይት ማቅረብ የፈለግኩት።

**የመቻቻል ባህል ማጎልመስ፦** ስንቶቻችን ነን የተለየ ሐሳብ ወይም ተጻራሪ አመለካከት የምንቀበል? ስንቶቻችን ነን የአስተሳሰብ ልዩነታችንን በኃይል ሳይሆን በጭውውት ወይም በውይይት (dialogue) ለመፍታት የምንመኩረው? በኔ አመለካከት የመቻቻል ባህል በሕበረተሰባችን ዘንድ ገና አልዳበረም። ይኸንን ርእሰ-ነገር አስመልክቶ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጽሑፎቼ አቅርብያቸዋለሁ፣ ወደ ዝርዝሩ ሳልገባም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች እርስ በራሳቸው የተጠፋፉት የመቻቻል ባህል ስለሌለን ነው በማለት አስምሬበት ነበር። አሁንስ? የመቻቻል ባህል በመሃከላችን ማጕልመስ እንችላለን ወይ? መልሱ አዎ ነው! የጠቢባን እምቅ ኃይል አለንና ነው! በሐሳብ ብቻ ሳይሆን በግብር መተርጎም እንቻላለን ወይ ለሚለው ጥያቄ ደግሞ 'ፍላጎት ካለ አዎ' ነው መልሱ።

ሆኖም ግን አብዛኛው በዳያስፖራ ያለው ኢትዮጵያዊ ከአንድነቱና የጋራ መለዮው (ኢትዮጵያዊነት) ወይም የጅምላ ባለታሪክነቱ ይልቅ በልዩነቱና በጎሳ አመለካከቱ

ላይ ስላተኰረ እንኳንስ የመቻቻል ባህል ሊያዳብርና አብሮ ለመብላትም የተሳነበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው፣ አብሮ ከበላም ወይ በሐዘን ወይም ደግሞ በሰርግ ጊዜ ብቻ ነው ማለት ይቻላል። ዞሮ ዞሮ አዝማሪው እንዳለው "አብሮ መብላት እንጂ ቀባሪ ማን ያውቃል" ነው ነገሩ። ባሁኑ ጊዜ በዳያስፖራ ያሉት ኢትዮጵያውያን፣ ከጥቂት በጣት የሚቆጠሩ በስተቀረ፣ የአንድ ኃይማኖት ተከታዮች ሆኖም አብረው በአንድ ጥላ ስር መጸለይ አልቻሉም (አልፈለጉም)፣ ስለሆነም የጠቢብነት ኃይላቸውን በገዛ ፈቃዳቸው አዳሽቀውታል ማለት ነው። አንዳንድ አንባብያን ይኸንን ሐተታ ካነበቡ በኋላ "ይህ ከሆነ ታድያ ኢትዮጵያውያን አንድነታቸውን ለመገንባትና ለመቻቻል እምቅ ኃይል የላቸውም ማለት ነው" ብለው ሊደመድሙ ይችላሉ። እኔ ግን "የለም አሁንም ቢሆን እምቅ ኃይሉ አለ፣ ፍላጎት ካለ እንደገና ማንሰራራት ይችላል" የሚል መልስ ነው የምሰጣቸው። የኢትዮጵያውያን እምቅ ኃይልና ፍላጎት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በተለያዩ ጊዜዎች ተከስቷል፣ ምሳሌዎች ለመጥቀስ ያህል፦ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን ለጎን በመሰለፍ የጣልያን ወራሪ ኃይልን ደመሰሰ፣ በማይጨው ጦርነትም አብሮ መከተ፣ በባብድመ ጦርነት ጊዜ ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክንዱን አስተባበረ፣ አሁን በቅርቡ በኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሳውዲ ዓረብያ በደረሰው ግፍ ምክንያት ደግሞ ዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን በዓለም ዙርያ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረግ ተቃውሞአቸውን አሳይቷል።

የመቻቻል ባህል ማኰልመስ ከፈለግን እንችላለን ነው መልሱ። የመቻቻል ባህል እንዲዳብር ከፈለግን ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ አራት የሕበረተሰባችን ክፍላተ-አካላት በዚሁ ረገድ ሐሳብ በማመንጨትና የመሪነት ሚና በመጫወት አርአያ መሆን አለባቸው። እነኚ አራት አካላት የሚከተሉት ናቸው፦ ሀ) የኢሕአዴግ መንግስት፣ ለ) ተቃዋሚ ፓርቲዎች በሃገርና በውጭ የሚገኙ፣ ሐ) ንቁ የፖለቲካ ተሳታፊ ምሁራን፣ መ) ድምጻቸውን ማሰማት የሚችሉ ኢትዮጵያውያን በሙሉ። ሁሉም ኃይሎች ሐላፊነቱን መሸከም አለባቸው፣ ነገር ግን በ ለ፣ ሐ፣ እና መ የተጠቀሱት አካላት ሥልጣን ስለሌላቸው የመቻቻልን መድረክ መምራት ያለበት ኢሕአዴግ ነው። እስካሁን ድረስ ያልተተገበረ ነገር ቢኖር ሃገራዊ እርቅ (national reconciliation) በሚል ርእስ ከዚህ ቀደም ያቀረብኩት ረቂቅ ነው። በሃገራዊ እርቅ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችና መንግሥት በውይይት ልዩነታቸውን እንዲፈቱና አብረው የሚሰሩበት መንገድ እንዲቀይሱ ሐሳብ አቅርቤ ነበር፣ ቢተገበር ኖሮ ደግሞ ሃገራችን ኢትዮጵያ ምን ያህል ትጠቀም ነበር።

**የኢትዮጵያ መጻኢ ዕድል በጋራ መወሰን፡-** ያገራችን ብሩህ ተስፋ እውን ለማድረግ ከፈለግን አሁንም ቢሆን በጠዋት ተነስተን ጠቢባን መሆናችንን ካረጋገጥን በኋላ አንድነታችንን ለመገንባት ደግሞ ጥረት ስናደርግ ብቻ ነው። አበው ነግረውናል! 'ድር ብያብር አንበሳን ያስር' ነው ነገሩ፣ ሌላ ብልሃት የለውም። ሁሉም አዋቂ ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው ጉዳይ ነው፣ የተሳነን ነገር ቢኖር በግብር መተርጎሙ ላይ ነው። ይኸንን አስመልክቶ ግን አብረን መስራት ያቃተን በዳያስፖራ ያለን ኢትዮጵያውያን እንጂ በሃገር ቤት ከሞላ ጎደል ሕዝቡ አብሮ እየሰራ ነው ያለው። ሕዝቡ በልዩ ልዩ መስኮች እየተሰማራ ነው፣ በርካታ የእርሻ፡ የኢንዱስትሪ፡ የትምህርትና የመሰረተ-ልማት ተቋማት ተዘርግቷል። ሕዝቡ በልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች እንደ የብሔሮች ቀን ወይም የከተሞች ሳምንት በመሳሰሉት በዓላትና ጉባኤዎች ላይ ተገናኝቶ ሐሳብ ለሐሳብ በመቀያየርና ለሃገር ልማት የሚጠቅሙ ንድፎችን በማውጣት በጋራ እየሰራ ነው። ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ያልነበሩትን መጠነ-ሰፊ መንገዶችና ሐዲዶች እንዲሁም በርካታ ዩኒቨርሲቲዎች ተገንብቷል፣ በቀጣይነትም እየተገነቡ ነው። አንድ ደካመ ጎን የምለው ነገር ቢኖር የዴሞክራሲ ባህል በኢትዮጵያችን ባለመዳበሩ ነው፣ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉም ሙስና ከመቸውም ጊዜ ስለተስፋፋ ትንፋሽን የሚያሳጥር አደገኛ መጥፎ

ባህል ተፈጥሯል ማለት ይቻላል። ሌሎች አያሌ ማሕበራዊ ችግሮችም አሉ፣ እነዚህን ችግሮች ለመዋጋት የሁላችን ሐላፊነት ቢሆንም ቅሉ መንግሥት ግን በይበልጥ ሐላፊነቱን መሸከም አለበት።

አሁን ባጠቃላይ ሲታይ ልማትን አስመልክቶ ኢትዮጵያ የያዘችው አቅጣጫ አመርቂ ነው። የኢትዮጵያ መጻኢ ዕድል ብሩህ እንዲሆን ከተፈለገ ግን በሃገራችን ሰፊ የዴሞክራሲ ባህል እንዲበለጽግ መሻት ይኖርብናል። በነገራችን ላይ፣ ዴሞክራሲ ማለት አንድ የመንግሥት ዘርፍ በጋራ መወሰን፣ የፓርላማ የሕዝብ ተወካዮች በድምጽ ብልጫ መወሰን ወይም ሕዝቡ በአምስት ዓመት አንዴ በምርጫ እንዲሳተፍና ድምጽ እንዲሰጥ ማድረግ ማለት ብቻ አይደለም። ዴሞክራሲ ማለት ምልአተ ሕዝቡ የመወሰን ችሎታ ሲኖረውና ያላንዳች ስጋት ሐሳቡን ለመግለጽ ሲችል ነው። ከሁሉም በላይ ግን የእውነት ዴሞክራሲ ሊነግስ የሚችለው ባለሥልጣኑ ለሕዝቡ ተጠያቂ ሲሆን ነው። ይህ ግን ባንዳፍታ የሚሆን ነገር አይደለም፣ ራሱን የቻለ የታሪክ ሂደት ስላለው የኢትዮጵያ የወደፊት ዕድል አስተማማኝ ይሆን ዘንድ ሁላችን የቻልነውን ያህል እናበርክት።

**ስነጽሑፍና የጽሑፍ ነጻነትን ማዳበር፦** የዴሞክራሲ አንዱ ገጽታ ዜጎች የመሰላቸውን ጽፈው ለሕዝቡ ሲያቀርቡት፣ ሕዝቡም በመሰለው ተርጉሞ ለጸሐፊዎቹ የተጠቃሚ አስተያየት ወይም ምላሽ ሲሰጥ ነው። የስነጽሑፍ መዳበር ደግሞ የአንድን አገር የልማት አቅጣጫ አስተማማኝነትን የሚያንጸባርቅ ነው፣ መንግሥት የስነጽሑፍ ነጻነት ከፈቀደ፡ ሁለ-ገብ ነጻነት ነው መሆን ያለበት። ጸሐፊዎቹ የመንግሥት ደጋፊዎች ሊሁኑ ይችላሉ፣ የመንግሥት ተቃዋሚዎችም ሊሆኑ ይችላሉ፣ መንግሥትን የማይወዱሱና የማይቃወሙ ደግሞ ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንዱ ደግሞ የመንግሥት ጠንካራ ጎኑና የሠራቸውን ስራዎች ሲያደንቁ በደካማ ጎኑ ደግሞ ሊወቅሱት ይችላሉ። መንግሥት ሁሉንም መቀበል አለበት። መንግሥት የመቻቻል መንገድን ከቀየሰ ደግሞ ሕዝቡ ሳይፈራ ሳይቸር የመናገርና የጽሑፍ ነጻነቱን በይበልጥ ያጐለምሳል፣ በግድ ሳይሆን በውድ መንግሥቱን ያቅፋል። ስለሆነም የኋላ ኋላ የጽሑፍ ነጻነትና ነቀፌታ መንግሥቱን ነው የሚጠቅመው።

ከዚህ ርእሰ-ነገር ጋር የሚያያዝ አንድ ጨዋታ ላጫውታችሁ። ድሮ የሆነ ነገር ነው። የአስራ አራት ዓመት ጨቅላ በነበርኩበት ጊዜ አጋጣሚ ሆኖ ንባብ የሚወዱ ቤተሰቦች ነበሩኝና ታላቁ ወንድሜ አንድ የኢትዮጵያ ባሕር ኃይል መጽሔት ይዞ ወደ ቤት ይመጣል፣ መጽሔቱን ከእጁ በመንጠቅ ማንበብ ጀመርኩኝ፣ መጽሔቱን ገለጥ ሳደርገው በሁለተኛው ገጽ ላይ “ነቀፌታ የማይቀበል መንግሥት ዘለቄታ የለውም” (ቀኃሥ) የሚል ጥቅስ ሳነብ እጅግ በጣም ተደነቅኩ፣ ንቃተ ኅሊናየም ያኔ ጀመረ ማለት እችላለሁ። ከሶስት ዓመት በኋላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን አጠናቀቅኩና አዲስ አበባ ዩኒቨሪሲቲ (ያኔ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨሪሲቲ) ገባሁ። ጃንሆይ ከቤተ መንግሥታቸው ወጥተው፣ ጢሞ እየመራቸው ወደሚሄዱበት ሲሄዱ ባየሁ ቁጥር ደግሞ ጥቅሱ ትዝ ይለኝ ነበር። በመጠኑም ቢሆን በጃንሆይ ጊዜ የስነጽሑፍ መዳበር እንጭጭነት ታይቶ ነበር ማለት ይቻላል። የእነ ሐዲስ አለማየሁ ‘ፍቅር እስከ መቃብር’፣ የአቤ ጉበኛ ‘አንድ ለናቱ’ እና ‘አልወለድም’፣ የማሞ ውድነህ ‘የኛ ሰው በደማስቆ’ ወዘተ ያነበብኩት ያኔ ነበር። በጃንሆይ መንግሥት መውደቅ ዋዜማ የተጻፈ ሌላ መጽሐፍ ‘የታሪክ ማስታወሻ’ ሆኖ ደራሲው ደጃዝማች ከበደ ተሰማ ናቸው። የጃንሆይን መንግሥት ቅልጥ አድርገው ስለሚወቅሱ ደግሞ ልጅ ሆኜ ያነበብኩትን ጥቅስ አውነትነት አለው ብየ ነበር። ነገር ግን በጃንሆይ ጊዜ ስመጥሩ ጸሐፊዎች እንደነ አቤ ጉበኛ እና አሳምነው ገብረወልድ ቀልጠው ሲቀሩና በተማሪዎች ደግሞ የግድያ እርምጃ ሲወሰድ የጥቅሱ ባዶነት ታየኝ።

ጃንሆይ አልፈው ጭራቁ ደርግ በሥልጣን ከተቆናጠጠ ወዲህ ደግሞ አገራችን ኢትዮጵያ በባሰ ሁኔታ በገሃነም ውስጥ ሰመጠች። እንኳንስ የስነጽሑፍና የመናገር ነጻነት ይኑርና ሕዝቡ በተነፈሰ ቁጥር የሞት ቅጣት ይበየንበት ነበር። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የራሱን ሕዝብ በአዋጅ ለማጨድ የተነሳሳ መንግሥት የደርግ መንግሥት ብቻ ነው። ስለዚህም፣ ግራም ነፈሰ ቀኝ የመቻቻልና የዴሞክራሲ ባህሎች ከልዳበሩ ወይ ተፋጦ ቁጭ ነው፣ ወይም ደግሞ መጠፋፋት ነው የሚሆነው ውጤቱ።

**መጽሐፍ መጽሐፍ በያለበት!** ይህ ርእሰ-ነገር የስነጽሑፍ ማበልጸግ ባህል ተቀጥያ ነው። የአፍ ታሪክ መልካም ነው፣ ግን ከጊዜ በኋላ ወይ ይቆራረጣል፣ ወይ ተጋኖ ይቀርባል ወይም ደግሞ ጠፍቶ ይቀራል። በጽሑፍ መልክ የተጠናቀረ ታሪክ ግን ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል፣ በዚሁ ረገድ ደግሞ እኛ ኢትዮጵያውያን ዕድለኞች ነን ማለት እንችላለን፣ ምክንያቱም የጥንት አባቶቻችን እና እናቶቻችን የምንከራባቸው የግእዝ ፊደላት ብቻ ሳይሆን በርካታ የታሪክና የኃይማኖት መጻሕፍት ጭምር አውርሰውን አልፈዋል። ጽሑፎቹ በብራና ብቻ የተጻፉ ሳይሆኑ በድንጋይም ሳይቀር የተወቀሩ ሰነዶች ለመሆናቸው አኵሪ ታሪካችንን በማስረጃነት ለማረጋገጥ ጠቅመውናል።

ያሁኑ ትውልድ ደግሞ ተመኩሮአችንን ለመጻፍ መረባረብ ይኖርብናል። ስነጽሑፍ ታሪክን መመዝገብ ብቻ አይደለም፣ ሰፊ ይዘት ያለው ሆኖ ከልብ ወለድ እስከ የትያትርና ድረማ ድርሰቶች፣ ከፖለቲካ ጽሑፎች እስከ ማሕበራዊ-ነክ ምርምሮች፣ ከሳይንስ ጽሑፎች እስከ ኃይማኖት-ነክ መረጃዎች ማቅረብ ሁሉ በስነጽሑፍ ውስጥ ሊጠቃለሉ ይችላሉ።

ቀደም ብየ እንደጠቀስኩት እኔና ጓዶኞቼ የተቻለንን ያህል እየጻፍን ነው ያለነው፣ ከኢትየጵውያን አንባብያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ደግሞ ብዙ ድጋፍ አግኝተናል። ሌሎች ከኛው ስብስብ ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ደራስያን ደግሞ ብዙ መጻሕፍት ያበረከቱ አሉ። እነዚህ ደራስያን እውቀቱና ችሎታውም ስላላቸው ምንጊዜም እነሱን ማበረታት ይኖርብናል። ከፍ ብየ በስማቸው የጠቀስኳቸውን ደራስያን አምስቱ ስለ ኢሕአፓ ነው የጻፉት፣ ከነዚሁም አንዱ ካሕሳይ አብርሃ ሲሆን ‘የዓሲምባ ፍቅር’ የሚል መጽሐፉን ለሕዝብ ካቀረበ በኋላ እኔ አቃቂር ጽፌለት ነበር፣ በመጽሐፉ ውስጥ አንዳንድ ግድፈቶች አሉ (የኔን ስም በጠቀሰው አከባቢ ጭምር)፣ ነገር ግን መጸሐፉ ብዙ መልካም የኢሕአሰን ታሪክ ስላጠናከረ በጠንካራ ጎኑ ላይ ለማትኮር ወሰንኩኝ፣ ስሕተቶችን ግን ለደራሲው በስልክ ከነገርኩት በኋላ እርሱም መታረም የሚኖሩባቸው ግድፈቶችን በሚቀጥለው እትም እንደሚያስተካክል ቃል ገብቶልኛን። ሌሎች ተችዎች ግን ከቅጡ ባለፈ መንገድ በደራሲው ላይ ውርጅብኝ ስለወረወሩ ቅር አሰኝቶኛል። ነቀፌታ መልካም፣ የማያስፈልግ የፖለቲካ ትርጉም እየሰጡ መተቸት ግን ተገቢ አይደለም። ከማንም ደራሲ ጋር በአንዳንድ ነጥቦች ላይ ላንስማማ እንችላለን፣ ግን ለመጻፋቸውና ለኢትዮጵያ ስነጽሑፍ ማበርከታቸው ብቻ ማመስገን ነው ያለብን። መጻሕፍቱ ደግሞ ቁዘማ ሳይሆኑ ነጸብራቆች ናቸው!

ጸሐየ ሰለሞን በ ‘ዓሲምባ ፍቅር’ ላይ ያቀረበውን ትችት ገንቢ ሆኖ ስላገኘሁት በዚሁ አጋጣሚ ላመሰግነው እወደላሁ። ጸሐየ ሒሳዊ ድጋፍ ካቀረበ በኋላ ከዚሁ ጽሑፍ ዋና ዓላማ የሚሄድ ቁምነገር ስለሰነዘረ መጥቀሱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፦ “ሁሉም የሚያውቀውንና የሚችለውን ቢጽፍ አሁንም ይመረጣል። ችሎታውና እውቀቱ ያላቸው ግለሰቦች የሚያውቁትን ታሪክ ሳያዛቡ ለንባብ

ማብቃት የጎላ ለመሆኑ መበረታታት አለበት እላለሁ። አሁንም በተለይ የታሪኩ የመጀመርያ ተጋሪዎች በቀሪ ዕድምያችሁ የምትችሉትን ፃፉና አስነብቡን፣ ለትውልድና ለሃገርም ታሪኩን አስቀምጡ” (ዓሲምባ ድረገጽ ኅዳር 13 2006)። ይህ ገንቢ አባባል ለዚሁ ጽሑፍ መግብያ ከጠቀስኩት ከ ታ ሆተፕ ጠቢብነት ጋር የሚሄድ ነው። ነገር ግን ጸሐየ ሰለሞን ከቀደምት ታጋዮችና አመራር ውስጥ ስለነበር አስነባቢ እንጂ አንባቢ ብቻ መሆን ስለሌለበት መጽሐፍ እንዲጽፍ ላበረታታው እወዳለሁ።

እንዲሁም ይኸንን አጋጣሚ በመጠቀም እያሱ አለማየሁን መጽሓፍ እንዲጽፍ ሐሳብ ላቀርብለት እወዳለሁ። በታሕሳስ 4 2006 እያሱ “እስቲ የነበርነው እንጻፍ! የኢሕአፓ ረጅም ትግል” በሚል ርእስ ድርሰት ደርሶ ነበር። እያሱ በጽሑፉ ላይ “የምናውቀው ሳንናገር የማያውቁት እየተንጫጩ ታሪክን ሊበርዙ እየጣሩ ናቸው” ይላል። ባንድ በኩል እያሱ ትክክል ነው፣ እኔ በበኩሌ በተማሪ ንቅናቄ ይሁን በማንኛውም የኢትዮጵያ የግራ ኃይል ትግሎች ውስጥ ያልተሳተፉ አዳዲስ ሐዋርያ መሳይ ጸሐፊዎች በተለያዩ ድረ-ገጾች ሲዘባርቁ ታዝብያለሁ። ይህ የሆነበት ምክንያት ግን አዋቂውና የነበረ ሳያጽፍ ስለቀረ አስመሳዩ መድረኩን ስለያዘ ይመስለኛል። ስለሆነም አስማማው ኃይሉ ስለ ኢሕአሰ በጻፈው መጽሐፉ ላይ ለምን መጽሐፉን ለመጻፍ እንደፈለገ ሲገልጽ “እውቀቱና ፍላጎቱ ያላቸውም ቢሆን ስላሳለፉት የትግል ታሪክና ሊያበርክት ስለሚችለው አስተዋጽኦ በተለያዩ ምክንያቶች ሊያሚሉ አለመቻላቸው” ይላል። እያሱም እውቀቱ ስላለው ከፓርቲውም መስራች አንዱ ስለሆነ መጸሐፍ ቢጽፍ የተሻለ ነው። ጽሑፉን ሲደመድም ግን ኢያሱ “ዝርዝር ታሪኩን ጊዜውን ይጠብቅ” ብለዋልና ዝርዝሩን በመጽሐፍ መልክ ቢወጣ የተሻለ ነው እላለሁ።

ስነጽሑፍ ማበርከት ግን እውቀትና ችሎታ ላላቸው ብቻ የሚተው አይደለም። አሁን በሰላሳ እና ሰላሳ አምስት ዓመት ክልል ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ለምሳሌ ኢሕአፓን ላያውቁት ይችላሉ። እድሜአቸው ከሃያ እስከ ሃያ ሦስት የሆኑት ወጣት ኢትዮጵያውያን ደግሞ ኢሕአዴግን ብቻ ሊያውቁ ይችላሉ። ከነዚህ ሁለት ስብስቦች አንዳንድ ግለሰቦች ስለግዜው ፓለቲካ መጽሐፍ ማበርከት ከፈለጉ ጥናታቸው በሌሎች ጽሑፎች ላይ በመንተራስ ስለሚሆን ተቀባይነት የለውም ማለት አንችለም። እንድያውም ወጣት ጸሐፊዎቹን ጥናታዊ ጽሑፎችን እንድያበረክቱ ማበረታታት ነው ያለብን።

**ሚዛናዊና ገንቢ ርእዮተዓለም መገንባት፡-** ማንኛውም ሕብረተሰብ ሚዛን ጠብቆ ከተራመደ የመረጋጋትና የልማት መንገዶችን ይቀይሳል፣ ሕብረተሰቡ በጽንፈኛ አመለካከት የተበከለ ከሆነ ደግሞ የኋላ ኋላ መውደሙ አይቀርም። ግለሰቦችና ስብስቦች ሚዛናዊ አመለካከት ካላቸው ለሃገራቸውና ለሕዝባቸው ገንቢ የሆኑ ጉዳዮችን ያበረክታሉ፣ ጽንፈኞች ከሆኑ ደግሞ ራሳቸውን ጎድተው ሕብረተሰባቸውን ይጎዳሉ። ሚዛናዊና አንጻራዊ አመለካከት እንዲኖረን ከተፈለገ ደግሞ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ከማጥናት በሻገር ከማሕበራዊ ስነሐሳቦች (social theories) እና ከታሪክ ክንውኖች (historical events) ጋር በማገናዘብ አጠቃላይና ሃገር-አቀፍ የሽግግርና የልማት ንድፎችን መቀየስ ይኖርብናል። ይኸንን አስመልክቶ፡ ባለው የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመንተራስ በአብነት ልንገልጸው እንችላለን።

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት የኢሕአዴግ መንግሥት የልማት ስትራተጂዎችን ነድፏል። በደፈናውና በጽንፈኝነት ተቃውሞ ከምናደርግ ደግሞ ሚዛን በመጠበቅ አስተያየት ወይም ነቀፌታ ብናቀርብ የተሻለ ይመስለኛል። ሚዛናዊና አንጻራዊ

አመለካከት በሰፊው ካየነው ደግሞ የአስተሳሰብ ዝንባሌ ብቻ ሳይሆን የታሪክ ክስተቶችን በጥሞና ማጤንና በዛውም መጠን ትክክለኛ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ንድፎችን በማውጣት መንቀሳቀስና ለሕብረተሰቡ ማበርከት ማለትም ነው። ከኢትዮጵያ አብዮት ፍንዳታ በፊትና በኋላ የኢትዮጵያ የግራ ኃይል ንቅናቄዎች የማርክስ ስነ-ሐሳብ ነበር የተከተሉት፣ ዋና ትኩረታቸውም በመደብ ትንታኔና አሰላለፍ እንዲሁም ጨቋኙን ሥርዓት በአብዮት ማስወገድ ላይ ነበር። ማርክስ "የሰው ልጆች የራሳቸውን ታሪክ ይሰራሉ፣ ግን እነሱ በመረጡት መንገድ አይሆንም" ላለው ግን ትኩረት አልሰጡትም። የዘመናችን ታሪክም የሚያሳየን ይኸው ነው፣ የዓለም አጠቃላይ ሁኔታ በፈለግነውና ባሰብነው መንገድ ሳይሆን በልገመትነውና ባላሰብነው መንገድ ነው የተጓዘው። በሌላ አገላለጽ የታሪክ አወድማዎች ይገዙናል ነው።

ለምሳሌ ባሁኑ ጊዜ በትጥቅ ትግል መንግሥት መቀየር የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ማኦ፣ ሆቺሚን እና ካስትሮ የቀየሱትንና በግብር የተጠቀሙበት የትግል ዘዴዎችን ባሁኑ ጊዜ መጠቀም አይቻልም። ጊዜው የሰላም ሽግግርን የሚጠይቅ ይመስላል፣ ስለሆነም በሕጋዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ቡድኖች በሥልጣን ላለው መንግሥት ከመርገምና ከመስደብ ይልቅ ሚዛን በጠበቀ መልኩ በመቃመውና በመውቀስ ቀዳዳዎች መፈለግ አለባቸው። ወይም ደግሞ ሁኔታው በፈቀደው መንገድ ምርጫ ሲካሄድ ሕዝቡን በማደራጀትና በማስከተት ለውድድር መቅረብና ለመንግሥት ሥልጣን መጋራት አለባቸው።

ሌላው መዘንጋት የሌለብን ነገር ቢኖር ከሁሉም ይልቅ ኢትዮጵያን ማስቀደም እናደለብን ነው። ሚዛናዊና አንጻራዊ አመለካከት ካደረግን ደግሞ ዘልአለማዊ የሚባል ሥርአት እንደማይኖር መገንዘብ እንችላለን፣ ሁሉም ነገር ያልፋል። መንግሥታት በታሪክ መድረኮች ላይ ብቅ ይላሉ ግን መድረኩን በዝንተአለማዊነት መቆጣጠር አይችሉም። ለምሳሌ አራቱ ነገስታትና አንድ ንግሥት (ቴዎድሮስ፣ የሐንስ፣ ሚኒሊክ፣ ዘውዲቱ እና ኃይለሥላሴ) በስልጣን ላይ ለተወሰኑ ጊዝያት ቆይተው የተቻላቸውን አድርጋው አልፈዋል፣ ኢሕአዴግም እንደዚሁ የተቻለውን አድርጎ ያልፋል፣ የመጪው መንግሥት ደግሞ እንደዚሁ፣ እኛም እንደዚሁ እናልፋለን። ኢትዮጵያ ግን የመጪውን ትውልድ ማስተናገድ ስላለበት ትቆያለች! ስለሆነም ለኢትዮጵያ ሃገራችንና ለመጪው ትውልድ አወንታዊ ስጦታ ማስተላለፍ የሁላችን ታሪካዊ ግዴታ ነው - ይኸም አዲሱ ርእዮተዓላማችን መሆን አለበት!

የባለቤትነት መብት የተጠበቀ ነው። አፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አልትተ)፣ ነሐሴ 2006. All Rights Reserved. Copyright © Institute of Development and Education for Africa (IDEA), 2014